A B Co.

**Abraham Berhanu**
Certified Audit Firm
**አብርሃም ብርሃኑ**
የተመሰከረለት ኦዲት ድርጅት

Off. 011 552 6200 | Mob. 091 122 0346 | Fax: 011 552 6185 | ✉ 101295
011 553 6686 | E-mail: abrahmberhanuco@gmail.com | Addis Ababa, Ethiopia

## ለኖኅተ ጥበብ ስክሲዮን ማህበር ስባላት የቀረበ የኦዲት ሪፖርት

### የቀረበ የኦዲት አስተያየት

የኖኅተ ጥበብ ስክሲዮን ማህበር ስ.ሴ.ስ ጁን 30 2021 ተዘጋጅተው የቀረቡልኝን የሂሳብ መግለጫዎች ማስትም የሀብትና ዕዳ፤ የትርፍና ኪሳራ፤ የገንዘብ ፍስትና እእንዲሁም ዋና ዋና የሂሳብ ፖሊሲዎችን መርምሬአለሁ::

በእኔ አስተያየት ቀጥሎ ከሚቀርበው አስተያየት በስተቀር የኩባንያው ሀብትና ዕዳ እ.ኤ.አ በጁን 30 ቀን 2021 የገቢና ወጪ ለተጠቀሰው ዓመት እእንዲሁም የገንዘብ ፍሰት የዓለም አቀፍ የሂሳብ አመዘጋገብ (አይ ኤፍ አር ኤስ) መሠረት በሚገባ (በትክክል) ያመለክታሉ::

### የታቀበ አስተያየት መሠረቱ

የሂሳብ ምርመራዬን የአለም አቀፍ የሂሳብ ምርመራ ደንብ በሚጠይቀው መሠረት አከናውኛለሁ:: የእኔ ኃላፊነት የሂሳብ ምርመራ የኦዲተሩ ኃላፊነት በሚለው ክፍል ውስጥ በዝርዝር ተቀምጧል:: እኔ በማንኛውም የጥቅም ግንኙነት ከኩባንያው ጋር ግንኙነት እንደሌለኝም እገልጻለሁ:: ይህም ድንጋጌ ዓለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች ጥምረት በሚጠይቀው የሥነ ምግባር ደንብ የተከናወነ ነው:: ይህንንም የሥነ ምግባር ደንቡ በሚጠይቀው መሠረት የተገበርኩ ሲሆን ለሥራዬ የሚያስፈልጉኝን ማንኛውንም ማስረጃዎች አግኝቻለሁ::

ኩባንያው በሊዝ ወስዶት የነበረውን ቦታ በስምምነቱ መሠረት በወቅቱ ግንባታ ባለመጀመሩ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ስምምነቱን ሰርዞታል:: ይህም በመሆኑ በመዝገብ ላይ የሚታየው የሊዝ ዋጋ በብር 11,092,019 የኩባንያውን ንብረት በዚሁ አኃዝ በይበልጥ እንዲታይ ሆኗል:: በሌላ በኩል በዕዳ የሚታየው የሊዝ ተከፋይ በብር 7,313,338 በይበልጥ እንዲታይ ተደርጓል:: በመሬቱ ላይ የወጣው ወጪ ብር 652,629 በዚሁ መሠረት የኩባንያውን ንብረት በይበልጥ እንዲታይ ሆኗል:: ይህ ወጪ ለአገልግሎት ስለማይውል በኩባንያው ሂሳብ ውስጥ መታየት አልነበረበትም:: ሆኖም ማኔጅመንቱ የክፍለ ከተማውን ውሳኔ ለማስቀልበስ ጥረት እያደረገ ነው::

### ዋና ዋና የሂሳብ ምርመራውን በተመለከተ

ዋና የሂሳብ ምርመራ ማለት በእኔ ሙያዊ አስተያየት ጉልህ ድርሻ ሊኖረው የሚችል ጉዳይ ነው:: ይህም የሂሳብ ምርመራውን በአጠቃላይ በተለይ የምርመራውን ውጤት በተለይ ያቀረብኩበት በተመለከተ ሲሆን በዚህ ክፍል የተለየ አስተያየት እንደሌለኝ እገልጻለሁ::